
# ያልታሰበው

## የሕይወቴ ፈታኝ ጉዞ እና
### የኢትዮጵያ አብዮት ተሳትፎዬ



ብርሃኑ ባይህ (ሌ/ኮሎኔል)

የኢትዮጵያ አካዳሚ ፕሬስ

# ያልታሰበው የሕይወቴ ፈታኝ ጉዞ
# እና
# የኢትዮጵያ አብዮት ተሳትፎዬ

ፕሬስ ከዚህ በፊት ያሳተማቸው መጻሕፍት

Dorothea McEwan Ethiopia Illustrated: Sacred Paintings, Maps and Drawings. (An Anthology) 2021 G.C
price 245 birr.

ዘለዓለም አንዳርጌ (ካፕቴን) *ፀሐይ፡ የኢትዮጵያ አቪዬሽን አጀማመር።* 2013 ዓ.ም.
ብር 235።

ማንይንገረው ሸንቁጥ። *ከደስታ ባለፈ፡ ተፈጥሯዊ የሩካቤ ሕይወት እና ውጤቱ።* 2012 ዓ.ም.።
ብር 140።

ሸብሩ ተድላ። *የሕያው ፈለግ።* 2010 ዓ.ም.።
ብር 126።

መንገሻ ሥዩም (ልዑል ራስ)። *የትውልድ አደራ።* 2010 ዓ.ም.።
ብር 170።

ኅሩይ ወልደ ሥላሴ፤ ባህሩ ዘውዴ (አሰናኝ)። *የኢትዮጵያ ልዑካን በአውሮጳና በመካከለኛው ምሥራቅ*
(1903)። 2009 ዓ.ም.።
ብር 150።

*ዝግመተ ለውጥ፣ አካባቢ እና ጤና በኢትዮጵያ።* የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ ገለጻ መድረክ።
2008 ዓ.ም.
ብር 60።

# ያልታሰበው የሕይወቴ ፈታኝ ጉዞ
# እና
# የኢትዮጵያ አብዮት ተሳትፎዬ

ብርሃኑ ባይህ (ሌ/ኮሎኔል)

2013 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

©የኢትዮጵያ አካዳሚ ፕሬስ፣ 2013 ዓ.ም.

የአሳታሚው መብቶች በሕግ የተጠበቁ ናቸው።

በዚህ መጽሐፍ የቀረቡ ሐሳቦች የደራሲውን አቋም የሚወክሉ ናቸው።

ISBN 978-99944-69-130

አንደኛው እትም 2013 ዓ.ም

የመጽሐፍ ሽፋን ንድፍና ሕትመት ኢክሊፕስ ማተሚያ ቤት። +251 115 572222/23

በኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ
የኢትዮጵያ አካዳሚ ፕሬስ
ፖ.ሣ.ቁ. 32228
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ስልክ +251 112 595 750
ኢሜይል eap@eas-et.org

# ማውጫ


የአሳታሚው ልዩ መግቢያ ........ ፲፯

መግቢያ (የደራሲው) ........ ፳

**ክፍል ፩** **1**

**ዕድገት፣ ትምህርት እና ወታደራዊ ሕይወት** **1**

**ምዕራፍ ፩** **2**

**ትውልድ እና ዕድገት** ........ 2

ትውልድ ........ 2

ወንድሞቼ እና እኅቶቼ ........ 6

የቤተሰቡ ጎጃም መግባት ........ 7

የሞጣው ዝውውር ........ 8

የትምህርት ጅማሮ ........ 10

**ምዕራፍ ፪** ........ **12**

**ኑሮ በሞጣ ከዘመድ አዝማድ ጋር** ........ 12

በአቶ ባይህ መሥሪያ ቤት የተከሠተ ችግር ........ 16

**ምዕራፍ ፫** **24**

**ፍኖተ ሰላም** ........ 24

የአበረ ይማም ዐመፅ ........ 27

**ምዕራፍ ፬** **33**

**ከጎጃም ውጭ ትምህርት** ........ 33

ሐረር የጦር አካዳሚ መግባት ........ 35

በጦር አካዳሚ የነበረው ውዝግብና ዐመፅ ........ 37

እስራት በአዲስ አበባ ........ 41

**ምዕራፍ ፭** **47**

**ወታደራዊ ቅጥቴን የፈጸምኩበት አካባቢ** ........ 47

የቅጣት ዘመን አመጋገብ ........ 51

በቅጣት ዘመን የሥራ ሥምሪት ........ 52

የ5ኛ ሻለቃ ከበብ ይዞት ........ 54

**ምዕራፍ ፮** **56**

**ድኅረ ቅጣት** ........ 56

የጀኔራል አማን ሚካኤል አንዶም ውሳኔ ........ 56

ለአቤቱታ ጉዞ ወደ አዲስ አበባ ........ 57

በአዲስ አበባው ውሳኔ አለመስማማት ........ 61

**ምዕራፍ ፯** **65**

**በአየር ወለድ ክፍል መመደብ** ........ 65

የአየር ወለድ ጦር ክፍል ኑሮ እና ሥልጠና ........ 65

የአየር ወለድ ሰፈር አስተዳደር ሥርዓት ........ 68

**ምዕራፍ ፰** **76**

**በአየር ወለድ ጦር ክፍል ሥምሪት** ........ 76

በሶማሊያ ጠረፍ አካባቢ መመደብ ........ 76

ከኦጋዴን ግጭት በኋላ የነበረኝ ሁኔታ ........ 84

ሞራል ግንባታ ........ 85

**ምዕራፍ ፱** **87**

**የኦጋዴን አካባቢ የጸጥታ ሁኔታ** ........ 87

የአንዳንድ የበላይ መኮንኖች ጠባይ ........ 88

**ምዕራፍ ፲** **106**

**በኦጋዴን ጦርነት ላይ በፈንጅ መቁሰል** ........ 106

ሕክምና በሐረር ጦር ሠራዊት ሆስፒታል ........ 111

ለዕረፍትና ለሕክምና ወደ አዲስ አበባ ........ 112

በሆስፒታል ከሌላ ታካሚ ጋር የተከሠተ ውዝግብ ........ 114

**ምዕራፍ ፲፩** **116**

**ዩኒቨርሲቲ ለመግባት የገጠመኝ ውጣ ውረድ** ........ 116

ዩኒቨርሲቲ ሬጅስትራር ቢሮ ........ 118

ዩኒቨርሲቲ እየተማርኩም ፈቃድ አለማግኘት ........ 119

የዩኒቨርሲቲ ትምህርት እና ኑሮ ........ 126

**ምዕራፍ ፲፪** **128**

**ዝውውር ወደ አሥመራ 2ኛ ክፍለ ጦር** ........ 128

ውዝግብ ከኮሎኔል ፈቃደ ጋር ........ 130

በተነቃናቂ ሕግ አስከባሪነቴ ያዘጋጀሁት የሥራ ፕሮግራም ........ 132

ባሕር ኃይል የጦር ፍርድ ቤት ስለሕግና ሕጋዊነት ..................... 132
ፈቃድ ጠይቄ ወደ መሐል አገር ሄድኩ..................... 140
ጉዞ ወደ ሞጣ ዘመድ ጥየቃ ..................... 141
**ምዕራፍ ፲፫** **143**
**ቤተሰብ ምሥረታና ማኅበራዊ ተሳትፎዎች** ..................... 143
ጋብቻ ..................... 143
ማኅበራዊ ተሳትፎዬና ትዝብቶቼ ..................... 146
**ምዕራፍ ፲፬** **151**
**ከ2ኛ ክፍለ ጦር ወደ ሐረር ጦር አካዳሚ መዛወር** ..................... 151
በዝውውር ወቅት የተከሠተ ችግር ..................... 151
**ምዕራፍ ፲፭** **156**
**በሐረር ጦር አካዳሚ የሥራ ሥምሪት** ..................... 156
በአካዳሚው የሥራ ድርሻዬ ..................... 156
በትምህርት ቤት ዲሬክተርነቴ የገጠሙኝ ተግዳሮቶች ..................... 157
ወታደራዊ ማዕረግ አሰጣጥ ሥርዓት ..................... 159
በሐረር ጦር አካዳሚ የማዕረግ ዕድገት ..................... 161
ሐረር የአካዳሚ በነበርኩበት ዘመን የወቅቱ የፖለቲካ ሁኔታ ..................... 163
በሐረር የጦር አካዳሚ የተፈጠሩ ችግሮች ..................... 165
**ምዕራፍ ፲፮** **167**
**የ1966 ዓ.ም. ወታደራዊ እንቅስቃሴ ዋዜማ** ..................... 167
የሠራዊቱ ተቃውሞዎች ..................... 167
የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ሆኜ የቀመስኩት ፖለቲካዊ አይታ ..................... 168
**ምዕራፍ ፲፯** ..................... **171**
**በአብዮቱ ዋዜማ 3ኛ ክፍለ ጦር የነበረው ሁኔታ** ..................... 171
ቅድመ ደርግ ..................... 171
ለሐረር ጦር አካዳሚ አዲስ አዛዥ መሾም ..................... 172
**ክፍል ፱** **177**
**የኢትዮጵያ አብዮትና ተሳትፎዬ** **177**
**ምዕራፍ ፲፰** **178**
**ለደርግ አባልነት መመረጥ** ..................... 178
የኢትዮጵያ ሥር ነቀል አብዮት ..................... 178

ስለ መንግሥት የነበረኝ አይታ ........ 183

**ምዕራፍ ፲፱** **187**

**የደርግ እና የመንግሥት ግንኙነት** ........ 187

በመረቀቅ ላይ የነበረው ሕገ መንግሥት ........ 187

በወቅቱ የተከሠቱ ሌሎች አሳሳቢ ጉዳዮች ........ 190

የወታደራዊ ተቋማቱ ወቅታዊ ሁኔታ ........ 193

የክቡር ዘበኛ ክፍለ ጦር ንኡስ ደርግ ዐመፅ ........ 194

የመሐንዲስ መምሪያ ዐመፅ ........ 195

ኅቡእ ድርጅቶች እና ሸኩቻቸው ........ 196

በመንግሥቱ ኃይለ ማርያም ላይ የተቃጣ የግድያ ሙከራ ........ 197

የኮንጎ ዘማቾች ጉዳይ ........ 199

**ምዕራፍ ፳** **200**

**ደርግ እና የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት** ........ 200

ሕገ መንግሥታዊ የዘውድ አገዛዝ ........ 200

ጀኔራል አማን ሚካኤል አንዶም የጦር ኃይሎች ኤታማጆር ሹም ሆነው መሾም ........ 202

የደርግ እና የንጉሠ ነገሥቱ የመጀመሪያ ግንኙነት ........ 203

የመንግሥት እና የደርግ የጋራ ኮሚቴ ........ 204

የደርግ የዕቅድ ኮሚቴ ተግዳሮቶች ........ 206

**ምዕራፍ ፳፩** **208**

**ደርግ እንደተቋቋመ የነበረው ፖለቲካዊ ውኅምብር** ........ 208

የተከሠቱ ችግሮች ........ 208

ከንኡስ ደርጎች የመነጩ ዕንቅፋቶች ........ 211

የደርግ ውስጣዊ ድርጅታዊና ፖለቲካዊ ይዘት ........ 214

**ምዕራፍ ፳፪** **216**

**መርማሪ ኮሚሽን ማቋቋም** ........ 216

ደርግና የመንግሥት ሚኒስትሮች ........ 216

የመርማሪ ኮሚሽንና የደርግ ግንኙነት ........ 219

በመርማሪ ኮሚሽኑ የዶክተር በረከት ሀብተ ሥላሴ ሚና ........ 220

**ምዕራፍ ፳፫** **223**

**የተጣረሰው የፖለቲካ እይታ** 223

የጀኔራል አማን አንዶም አመራር ........ 223
የደርግ እና የጀኔራል አማን ቅራኔ ........ 224
የጀኔራል አማን የኤርትራ ጉብኝት ........ 226
የጀኔራል አማን ኩርፊያ እና የደርግ ምልጃ ........ 231

**ምዕራፍ ፳፬** **240**

**ሥር ነቀል የፖለቲካ እርምጃና አሰቃቂ ድርጊቶች** 240
ንጉሠ ነገሥቱን ከሥልጣን ማውረድ ........ 240
የንጉሠ ነገሥቱ ሹማምንት ዕጣ ፈንታ ........ 241
በቀድሞ ሹማምንት ላይ የተወሰደ አሳዛኝ እርምጃ ........ 244
የጀኔራል አማን አንዶም ዕጣ ፈንታ ........ 250

**ምዕራፍ ፳፭** **252**

**የዕድገት በኅብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ** ........ 252
ቅድመ ዘመቻ ........ 252
የ"ኢትዮጵያ ትቅደም" ዓላማና የዘመቻ ቅስቀሳ ........ 253
የዩኒቨርሲቲ መምህራን አስተያየት እና የተማሪዎች ዘመቻ ........ 259
የሶሻያሊዝም ርእዮተ ዓለም ጥናት ሂደት ........ 262

**ምዕራፍ ፳፮** **263**

የገጠር መሬት ረቂቅ ዐዋጆችና ያስከተለው ውዝግብ ........ 263
የገጠር መሬትን በዐዋጅ ለአራሹ ማስረከብ ........ 263

**ምዕራፍ ፳፯** **275**

**የከተማ ቦታና ትርፍ ቤቶች እንዲሁም የበዓላት ዐዋጆች** ........ 275
የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት ዐዋጅ ረቂቅ ........ 276
ረቂቅ ዐዋጁ ያስከተለው ክርክር ........ 276
አዳዲስ ብሔራዊ በዓላትን መሰየም ........ 278

**ምዕራፍ ፳፰** **280**

**በዐዋጆች መንሥኤ የተከሠቱ ዐመፆች** ........ 280
የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረት /ኢዲዩ / ኢዴኅ/ ........ 280
በጅማ አካባቢ በዘማቾችና በአካባቢው አስተዳደር መካከል የተከሠተ ችግር ........ 281
የፖሊስ አቋም ........ 282

**ምዕራፍ ፳፱** **295**

**ደርግ እየተደላደለ ሥራውን ቀጠለ** ........ 295

ደርግ የስብሰባ ቦታውን ቀየረ ........ 295

አዲስ ጠቅላይ ሚኒስትር መሠየም ........ 297

የኮንን ዘማቾች ጥያቄ ........ 301

የደርግ አባሎች ኑሮ ........ 303

የጤናዬ መታወክ ........ 303

**ምዕራፍ ፴** **307**

**ስለ ኤርትራ የግል ግንዛቤዬና የነበረኝ ሐላፊነት** ........ 307

ቅድመ ደርግ ስለ ኤርትራ የነበረኝ ግንዛቤ ........ 307

ደርግ እንደተቋቋመ በኤርትራ የነበረኝ የፖለቲካ ሐላፊነት ........ 310

ከኤርትራ ሽማግሌዎች ጋር የተደረገ ውይይት ........ 312

**ምዕራፍ ፴፩** **326**

**የውጭ ግንኙነት** ........ 326

በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስተባባሪነት የተካኼደ ስብሰባ ........ 326

ደጃዝማች ዘውዴ ገብረ ሥላሴ ........ 327

የዐረብ አገሮች ጉብኝት ........ 329

ጉዞ ወደ ቡልጋሪያ ........ 337

**ምዕራፍ ፴፪** **339**

**እንደገና ወደ አሥመራ** ........ 339

ጉዞ ወደ ሲሪላንካ ........ 344

ጉዞ ወደ ዐረብ አገሮች ........ 347

**ምዕራፍ ፴፫** **348**

**በኢሕአፓ የተጠነሰሱ ተንኮሎች** ........ 348

ሐሰተኛ የደመወዝ ጭማሪ ወሬ ........ 348

ሐረር በሠራዊቱ አባላት ስብሰባ ላይ የተከሠተ ውዥምብር ........ 353

**ምዕራፍ ፴፬** **358**

**ሕዝባዊ ዐመፆች እና ወታደራዊ ችግሮች** ........ 358

ሠራዊቱ ውስጥ የነበረው አስቸጋሪ ሁኔታ ........ 359

ጎጃም እና ሸዋ ውስጥ የነበሩ ዐመፆች እንደ ምሳሌነት ........ 359

በተማሪዎችና በሠራተኞች የተጠነሰሰ የከተሞች ችግር ..... 364

**ምዕራፍ ፴፭** **369**

**የደርግ አጠቃላይ ፖለቲካዊ ይዘት** ..... 369

የሕዝብ አደራጅ ኮሚሽን መመሥረት ..... 372

የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽሕፈት ቤት ማቋቋም ..... 374

**ምዕራፍ ፴፮** **377**

**በደርግ አባላት መካከል መቃቃር መፈጠር** ..... 377

በደርግ አባላት ይስነዘረብኝ የነበረ የዐመፅ ቅስቀሳ ..... 378

የሻለቃ ሲሳይ መወንጀል፣ ..... 382

የጀኔራል ጌታቸው ናደው መገደል ..... 384

የተለያዩ ውንጀላዎችና የፍርድ ቤቶች ፍትሕ አሰጣጥ ..... 384

አዲስ የፍርድ ተቋም ..... 387

በደርግ አባላትና በሌሎች ላይ የቀረበ ክስ እና የተሰጠ ፍርድ ..... 388

**ምዕራፍ ፴፯** **392**

**የኤርትራ አሳሳቢ ጉዳይ እና የተከሠቱ ልዩ ልዩ ሁኔታዎች** ..... 392

የአሰብ ጦር ዐመፅ ..... 398

እንደገና ወደ ኤርትራ ጉዞ ..... 401

የፒቲ ኦፊሰር ሚካኤል አስገዶም መገደል ..... 402

**ምዕራፍ ፴፰** **405**

**በወቅቱ የተከሠቱ የተለያዩ ችግሮችና የመፍትሔ ፍለጋ** ..... 405

የደርግ ውስጣዊ እና ከውጭ የመነጩ ችግሮች ..... 405

ለደርግ ውስጣዊ ችግር መፍትሔ የታሰበ መዋቅር ..... 406

ከዋናው ሊቀ መንበር ጋር መቃቃሬ ..... 415

የአዲሱ ቋሚ ኮሚቴ የመጀመሪያ ስብሰባ ..... 416

**ምዕራፍ ፴፱** **418**

**አዲሱ የደርግ መዋቅር ያስከተለው ችግር** ..... 418

በአዲሱ መዋቅር የሥልጣን ሽኩቻ ..... 419

የመንግሥቱ አምባ ገነንነት እየጎላ መሄድ ..... 421

ጀኔራል ተፈሪ በንቲ የገቡበት አጣብቂኝ ..... 423

በሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጽሕፈት ቤት የታቀደ ፀረ ኢሕአፓ ሰልፍ ውጤት ..... 425

**427**
**ምዕራፍ ፵**
**የመንግሥቱ ኃይለ ማርያም ሤራ** ........ 427
በደርግ አባላት መካከል የተፈጠረው አለመተማመን እና ውጤቱ ........ 427
በደርግ አባላት ላይ የተወሰደ እርምጃ ........ 428
በደርግ ቋሚ ኮሚቴ አባላት ላይ የተወሰደ እርምጃ ........ 433
የእነ ሠናይ ልኬ መገደል ........ 435
**435**
**ምዕራፍ ፵፩**
**አዲስ ቋሚ ኮሚቴ እና አሰቃቂ የወጣቱ ጭፍጨፋዎች** ........ 435
እንደገና አዲስ ቋሚ ኮሚቴ መሠየም ........ 435
የሌ/ኮሎኔል አጥናፉ አባተ መገደል ........ 436
የእርስ በርስ ግድያ፤ ቀይ ሽብር፣ ነጭ ሽብር ........ 437
የቀበሌ ካድሬዎችና የኢሕአፓ ፍልሚያ ........ 439
የአራት ኪሎው ግርማ ከበደ ........ 439
**443**
**ምዕራፍ ፵፪**
**በኢትዮጵያና በሶማሊያ መካከል የነበረውን ቅራኔ የመፍታት ጥረት** ........ 443
አብዮቱ ሲፈነዳ የነበረው ዓለም አቀፍ ተጨባጭ ሁኔታ ........ 443
የኩባው አምባሳደር ፔፔ ........ 444
ከሶማሊያ ጋር ስምምነት ለማስፈን በየመን የተደረገ ስብሰባ ........ 445
የአገር መከላከል ዝግጅት ........ 446
የርእሰ ብሔሩ የመጀመሪያው ኦፊሴል ጉብኝት በሶቭየት ኅብረት ........ 446
የአብዮታዊ ሰደድና በፓርቲው አካባቢ የተከሠቱ ችግሮች ........ 448
ከኃይሌ ፊዳ ጋር የነበረኝ መጠነኛ አለመግባባት ........ 449
**452**
**ምዕራፍ ፵፫**
**የእናት አገር ጥሪ** ........ 452
ክተት በየፈርጁ ........ 452
የጦር መሣሪያ ድጋፍ ........ 455
የእናት አገር ጥሪ ውጤት፤ የሠራዊቱ ሰልፍ ........ 456
የሠለጠነው ሚሊሻ ሥምሪት ........ 462
የኩባውያንን ውለታ ለመክፈል የተደረገ ጉዞ ........ 464
**469**
**ምዕራፍ ፵፬**
**የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ስብሰባ በሊቨርቪል** ........ 469

**ምዕራፍ ፴፭** **475**

**በሶማሊያ የተቀሰቀሰው ጦርነትና ውጤቱ** ........ 475

በአየር ኃይል ተሳትፎ የደረሰ አደጋ ........ 475

በወቅቱ ኢትዮጵያንና ሶማሊያን ለማስታረቅ የታቀደ ሽምግልና ........ 477

ወረራው በየአቅጣጫው ቀጠለ ........ 478

የሐረርና ድሬዳዋ ለጠላት ወረራ መጋለጥ ........ 482

ከመንግሥቱ ጋር አለመግባባት ........ 484

በኤርትራ ግንባር ፍልሚያ ........ 486

**ምዕራፍ ፴፮** **489**

**የሶቭየት ኅብረት እርዳታ** ........ 489

የጦር መሣሪያ ከሶቭየት ኅብረት ወደ ኢትዮጵያ ማጓጓዝ ተጀመረ ........ 489

በሶማሊያ ግንባር ጦርነቱ ተጠናክሮ ቀጠለ ........ 491

ጦሩ ግንባሩን በተጠናከረ መልክ ወደ ሰሜን ማዞር ........ 492

በጦርነቱ ወቅት የኩባ መንግሥት ድጋፍ ........ 495

የኩባ ጦር ወደ ኢትዮጵያ መግባት ........ 497

**ምዕራፍ ፴፯** **499**

**ከሶማሊያ ጋር ዕርቅ የማስፈን ተጨማሪ ሙከራ** ........ 499

የተለያዩ መንግሥታት የዕርቅ ሙከራዎች ........ 499

ከሰሜን መጥፎ ዜና ተሰማ፤ ጉዞ ወደ ኤርትራ ........ 500

የመኢሶን መሪዎች መሰወር ........ 505

**ምዕራፍ ፴፰** **509**

**ከሶማሊያ ጋር የሻከረው ግንኙነት እና ዕርቅ** ........ 509

በአገር ቤት ሥጋት በየፈርጁ ........ 511

መልሶ ማጥቃት ........ 516

የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት የሽምግልና ኮሚቴ መልእክት ........ 519

**ምዕራፍ ፴፱.** **522**

**በወቅቱ የነበረው የኤርትራ ጦርነት ሁኔታ** ........ 522

በምሥራቅ ጀርመን የተሞከረ የዕርቅ ድርድር ........ 522

በርሊን ከእነ ኢሳይያስ አፈወርቂ ጋር የተደረገው ስብሰባ ሂደት ........ 523

**ምዕራፍ ፵** **530**

**የአብዮት በዓል እና የአገር ውስጥ ፖለቲካዊ ሁኔታ** ........ 530

የጣምራ በዓል ዝግጅት ....................

አራተኛው የአብዮት በዓል መከበር ....................

የፊደል ካስትሮ ጉብኝት ....................

የፖለቲካ ፓርቲዎች ሽኩቻ ....................

የደርግ አባላት እርስ በርስ መካሰስ ....................

**ምዕራፍ ፶፩**

**የውጭ አገር ጉብኝቶች** ....................

**ምዕራፍ ፶፪**

**በደርግ አባላት መካከል የተከሠተ ውዝግብ** ....................

የቋሚ ኮሚቴ አባላትን ለማጋጨት የተሸረበ ተንኮል ....................

**ምዕራፍ ፶፫**

**የአፍሪቃ ጉዳይ** ....................

ዚምባብዌ "ደቡብ ሮዴዥያ" ....................

ሙጋቤንና ንኮሞን የማስታረቅ ሙከራ እና ጦር ማሠልጠን ....................

**ምዕራፍ ፶፬**

**የአገር ቤት ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች** ....................

አዲስ የፖለቲካ መዋቅር ....................

የኢሠፓአኮ መሥራች ጉባኤ (ሰኔ 1972 ዓ.ም.) ....................

የኢሠፓ ምሥረታ ዝግጅት ....................

**ምዕራፍ ፶፭**

**ከሱዳን ጋር የተመሠረተው አዲስ ግንኙነት** ....................

ከሱዳን የመጣ መልእክት ....................

የኢትዮጵያ እና የሱዳን መሪዎች ጉብኝት ....................

የኢትዮጵያ እርዳታ - ለደቡብ ሱዳን ዐማፅያን ....................

**ምዕራፍ ፶፮**

**በኢሠፓ ምሥረታ ዋዜማ የተከሠተ ድርቅ** ....................

ሰፈራ ....................

ቁጠባን መሠረት ያደረጉ መንግሥታዊ ውሳኔዎች ....................

የደንብ ልብስ ....................

**ምዕራፍ ፶፯**

**የደርግ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ሹም ሽር** ....................

የእኔና የመንግሥቱ መጠነኛ መቃቃር ........................................ 611

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሆኜ መሾም ........................................ 616

በደርግ ሥልጣን ማከተሚያ ላይ የተሰጠኝ ሹመት ........................................ 618

**ምዕራፍ ፶፯ ........................................ 620**

**በወቅቱ ከሶማሊያ ጋር የነበረው ግንኙነት** ........................................ 620

ጉዞ ወደ ሶማሊያ ........................................ 621

በሶማሊያ የኢትዮጵያን አምባሳደር መሾም ........................................ 623

**ክፍል ፫ 625**

**የአብዮቱ ምሽት 625**

**ምዕራፍ ፶፰ 626**

**የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ** ........................................ 626

ሠራዊቱ በፓርቲው እና በመንግሥት ላይ የነበረው እምነት ........................................ 626

ዐመፁን በማክሸፍ የመንግሥቱ ገመቹ ሚና ........................................ 633

የዐመፁ ተባባሪዎች በአሥመራ ........................................ 636

መፈንቅለ መንግሥት ለማድረግ የሞከሩት ላይ የተወሰደ እርምጃ........ 641

**ምዕራፍ ፶፱ 642**

**በአብዮቱ ማከተሚያ የተከናወኑ ተግባራት** ........................................ 642

የግል ሹመት ........................................ 642

ስለጦርነቱ ከመንግሥቱ ጋር በግል የተደረገው ውይይት ........................................ 643

አዲስ የዘመቻ ቀጠናዎች ማዋቀር ........................................ 643

አስቸኳይ ልዩ ስብሰባዎች ........................................ 644

የብሔራዊ ሸንጎ ሦስተኛ አስቸኳይ ስብሰባ ........................................ 647

የብሔራዊ ሸንጎ ውሳኔዎች ........................................ 649

የመንግሥት ምክር ቤት ስብሰባ ........................................ 650

**ምዕራፍ ፷ 656**

**አዲስ የመንግሥት መዋቅር** ........................................ 656

ብሔራዊ ዘመቻ ........................................ 656

የመንግሥቱ ኃይለ ማርያም መኮብለል ........................................ 656

የሰሞኑ የአዲስ አበባ ሁኔታና ውጥረት ........................................ 664

የመጨረሻው ሰዓት ........................................ 666

የደርግ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ውሳኔዎች ........ 666

ሥርዓት አልበኝነት በቤተ መንግሥት ........ 668

**671**

**ምዕራፍ ፳፩** ........ 671

**"ጆሮ ለባለቤቱ ባዳ ነው"** ........ 674

በአልፈጸምኩት ተግባር መታማት ........ 677

ባላሰብኩት መንገድ የተንኮል ተባባሪ መደረግ ........ 679

ከአንዷት የሟች ባለቤት የተሰነዘረብኝ ወቀሳ

**682**

**ምዕራፍ ፳፪** ........ 682

**ስደት በሀገር ውስጥ** ........ 682

ረዢሙ የጥገኝነት ኑሮ ........ **694**

**መጠቁም**

# የአሳታሚው ልዩ መግቢያ

እስካሁን የኢትዮጵያ አካዳሚ ፕሬስ ካሳተማቸው መጻሕፍት፣ ይህ ጽሑፍ ለየት ያለ ታሪክ ስላለው፣ ገለጻውን በዚህ መግቢያ ማቅረብ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ጸሐፊው ሌ/ኮሎኔል ብርሃኑ ባይህ እንግዳ፣ የደርግ አባል በነበሩበት ዘመን፣ የተለያዩ የመንግሥት የሐላፊነት ቦታዎች ተሾመው አገራቸውን ማገልገላቸው ይታወቃል። የደርግ መንግሥት በፈረሰበት ወቅት ጣልያን ኤምባሲ ውስጥ ከተጠለሉት ጥቂት የደርግ ባለ ሥልጣናት አንዱ ነበሩ። ስለሆነም ደርግ ከሥልጣን ከወረደበት ከግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ታኅሣሥ 27 ቀን 2013 ዓም ድረስ፣ ወደ ሠላሳ ዓመት ለሚጠጋ ጊዜ፣ በጥገኝነት ጣልያን ኤምባሲ ውስጥ ቆይተዋል። ምንም እንኳን ኤምባሲው ውስጥ ለዘመናት ቢቀመጡም፣ «እነሱን ለመጠየቅ አይቻልም» የሚለው መረጃ መሻሩን ባለማወቅ፣ እሳቸውን እና ሌላኛውን የአገር ቤት ስደተኛ፣ ጀነራል አዲስ ተድላን ለመጠየቅ እንደሚቻል ወዳጅ ዘመዶቻቸው የተረዱት ከዓመታት በኋላ ነበር። በዚህ ጊዜ ከጠያቂዎቹ አንዱ (ፕሮፌሰር ሽብሩ ተድላ) ኮሎኔል ብርሃኑ ባይህ ስለ ሕይወት ጉዟቸው የመጽሐፍ ረቂቅ ማዘጋጀታቸውን ለማወቅ በቁ፣ እንደዚሁም፣ ከጀነራል አዲስ እና ከጀነራል ተስፋዬ ገብረ ኪዳን ጋር በመሆን አጠቃላይ የአብዮቱን ሂደት የሚተርክ የመጽሐፍ ረቂቅ እና ጀነራል አዲስ የጻፉት የሕይወት ታሪካቸው እንዳለ ተረዱ። ፕሮፌሰር ሽብሩ ቅርበታቸው ለኮሎኔል ብርሃኑ ስለነበር፣ የመጀመሪያ ትኩረታቸውን ያደረጉት የኮሎኔል ብርሃኑ ባይህ ረቂቅ ጽሑፍ ላይ ነበር፤ የጽሑፉን "ኤሌክትሮኒክ" ቅጅ ለማንበብ ባለቤቱን ፈቃድ ጠይቀው፣ ቅጂውን ከኤምባሲው ለማውጣት ቻሉ። የዚህ መጽሐፍ ባለታሪክ (ብርሃኑ ባይህ) ተግባር ተኮር ግለሰብ መሆናቸውን ስለሚያውቁ እና ያዘጋጁት ጽሑፍ ጠቀሜታ ይኖረዋል ብለው ስለገመቱ፣ ጊዜ ወስደው በጥሞና አነበቡት፤ ጽሑፉም ጠቀሜታ እንዳለው እርግጠኛ ሆኑ። እጅግ ብዙ ጉዳዮች የተተረኩበት ጽሑፍ ቢሆንም፣ ረቂቁ 2105 ገጽ ስለሆነ ለማንበብም ሆነ ለማሳተም አስቸጋሪ እንደሚሆን ገመቱ፡፡ ብዙ ዝርዝር ጉዳዮችን የያዘ በመሆኑ ቢታተም ትልቅ ጠቀሜታ እንደሚኖረው ባያጠያይቅም፣ እንዴት ሊታተም ይችላል የሚለው ጥያቄ ግን በቀላሉ መልስ ሊሰጠው አይቻልም፡፡ በወቅቱ የኢትዮጵያ የሳይንስ አካዳሚ አሳታሚ ፕሬስ ለማቋቋም የሚያደርገውን ዝግጅት እያጠናቀቀ ስለነበር እና እርሳቸውም የድርጅቱ አባል ስለሆኑ፣ ጉዳዩን ወደ ሐላፊዎቹ ለመውሰድ ወሰኑ፡፡

ከዚያም ረቂቁን ለአካዳሚው የሥራ አስፈጻሚ ዳይሬክተር ለፕሮፌሰር ማስረሻ ፈጠነና በወቅቱ እየተቋቋመ ያለው ፕሬስ ሀላፊ ለነበሩት ለአቶ ብርሃኑ ደቦጭ (የታሪክ ምሁር) በመስጠት አስተያየታቸውን ጠየቁ፡፡ ሦስተኛ ሐሳብ ለማግኘት ፕሮፌሰር ሽፈራው በቀለን (የታሪክ ምሁር እና የአካዳሚው አባል) አንብበው አስተያየት እንዲሰጡበት ጠየቋቸው። ሦስቱም ሰዎች ጊዜ ሳይፈጁ፣ ከሁለት ሺሕ በላይ ገጾች የነበረውን ረቂቅ አንብበው፣ ጽሑፉ ቢታተም ለታሪክ ጥናት ብዙ ጠቀሜታ እንደሚኖረው ገለጹ። ለምሳሌ በጽሑፍ ከቀረቡት ግምገማዎች መካከል፣ ፕሮፌሰር ሺፈራው የሰጡትን አስተያየት ቀንጭበን እናቀርባለን፦

> ይህ ጽሑፍ... ጠቃሚ የሆነ ሰነድ ነው ብሎ መደምደም ይቻላል። ምክንያቱም እስከ አሁን የማናውቃቸውን ብዙ ነገሮች ስለሚያሳውቀን እና ከዚህ በፊት የምናውቃቸው ጉዳዮች ከሆኑም ስለሚያጠናክራቸው፣ ወይም ስለሚቃረናቸው ነው። መጽሐፉን በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል። ክፍል አንድ እስከ ደርግ መቋቋም ድረስ ያለው የጸሐፊው ትውስታ ሲሆን፣ ክፍል ሁለት የደርግ ዘመን ይሆናል።

ሁለቱም ዋጋ አላቸው። ሁለቱም ክፍሎች ... ለታሪክ ተመራማሪው ብዙ መረጃ ይሰጣሉ። የመጀመሪያው ክፍል ማለትም ቅድመ ደርግ ክፍል ለሁለተኛው ክፍል ታሪካዊ ዐውዱን (historical context) ይሰጠዋል። በዚህ የተነሣ ኋላ ላይ ትላልቅ የፖለቲካ ወይም ወታደራዊ ሥልጣን ይዘው በሀገር ደረጃ ትልቅ ሚና የሚጫወቱ ግለሰቦችን በወጣትነታቸው እናገኝበታለን፡- ጌታቸው ናደው፣ ደምሴ ቡልቱ፣ ተፈሪ ተክለ ሃይማኖት፣ ወዘተ...፤ ከጀነራሎችም ቢሆን አንዳንዶቹን ቀድመን እንተዋወቃቸዋለን፡-ጀኔራል አማን ሚካኤል አንዶም፣ ጀኔራል ነጋ ተገኝ ሊጠቀሱ ይችላሉ። ስለዚህ የመጀመሪያው እና የሁለተኛው ክፍል አንድ አምሳል ናቸው ማለት ይቻላል። የዚህ ትውስታ ትልቅ አስተዋጽዖ በስፋት መቅረቡ፣ ብዙ ጉዳዮችን በዝርዝር ማየቱ ነው። በዚህ የተነሣ ... ብዙ ቁም ነገሮች ተዳስሰውበታል። እስከ አሁን ከታተሙት የትዝታ መጻሕፍት ጋር፡- ማለት ከመንግሥቱ ኃይለማርያም፣ ከፍቅረ ሥላሴ ወግደረስ እና ከፍስሐ ደስታ ሥራዎች ጋር ሲወዳደር - ይሄኛው በሚያቀርበው ዝርዝር ምክንያት ልቆ ይገኛል።... ጽሑፉ ገና ለኅትመት አልደረሰም፣ ሰፊ የአርትዖት ሥራ ይቀረዋል።

የደርግ አባል በነበሩባቸው ጊዜያት፣ ኮሎኔል ብርሃኑ ማስታወሻ ይይዙ እንደነበር ከጽሑፉ ማወቅ ይቻላል፤ ነገር ግን፣ ደርግ ሲወድቅ እና ወደ ኢጣልያን ኤምባሲ በሄዱበት ወቅት ቤታቸው ደረስ ብለው ሁሉንም ማስታወሻ ደብተሮቻቸውን ይዘው ማምለጥ አልቻሉም፤ እርግጥ ነው ረዳታቸው ደብተሮቻቸውን ቤታቸው ሄዶ ቢያመጣላቸውም ሁሉንም ስላልነበር ያመጣው፣ አንዳንዶቹን ምዕራፎች ሲጽፉ መቸገራቸው አልቀረም፡፡ቢሆንም፣ አብዛኛው ትውስታ በዝርዝር የተሞላ ነው፡፡ ያም ሆነ ይህ፣ እንዴት ይታተም የሚለው ከባድ ጥያቄ ነበር፡፡ በዚያን ወቅት፣ የአካዳሚው ፕሬስ ገና አማካሪ ቦርድ ስላልተሰየመለት፣ ለውሳኔ እንዲያመቻቸው፣ ፕሮፌሰር ማስረሻ አንድ ኮሚቴ አቋቋሙ። የኮሚቴውም አባላት ራሳቸው ፕሮፌሰር ማስረሻ ፈጠነ (ሰብሳቢ)፣ ፕሮፌሰር ሽፈራው በቀለ (አባል)፣ ፕሮፌሰር ሽብሩ ተድላ (አባል) እና አቶ ብርሃኑ ደቦጭ (ጸሐፊ) ነበሩ። የኮሚቴው ዋና ተግባር ረቂቁን ባለበት መልኩ ለማተም ከወጭም አንጻር፣ ከአንባቢም አንጻር የማይመከር ስለሆነ፣ ምን ሌላ አማራጭ ይኖራል ለሚለው ጥያቄ መልስ መስጠት ነው፡፡

ከብዙ ውይይት በኋላ፣ ኮሚቴው ረቂቁን እንዳለ ከማሳተም፣ ብዙዎቹን ዝርዝሮቹን አውጥቶ አጠር ያለ (የፈረንጅ አሳታሚዎች እንደሚሉት abridged የሆነ) የትዝታ መጽሐፍ ማውጣት ይሻላል ብሎ ከወሰነ በኋላ ዋናው ጽሑፍ ግን በሥነ ሥርዓት በሁለት ቅጅዎች ተዘጋጅቶ ተመራማሪዎች እንዲጠቀሙበት፣ አንዱ ቅጅ በኢትዮጵያ ጥናት ተቋም ክምችት ውስጥ፣ ሌላው ደግሞ በአካዳሚው ቤተ መጻሕፍት ውስጥ እንዲቀመጥ የሚል ምክር ለሥራ አስፈጻሚ ዲሬክተሩ አቀረበ፡፡ በዚህ ሀሳብ መሰረት፣ ፕሮፌሰር ሽብሩ አንዱን ቅጅ ለኢትዮጵያ ጥናት ተቋም እና ሌላውን ለአካዳሚው አስረከቡ፡፡ ማሳጠሩን ለመሥራት ተመራጭ ይሆን የነበረው፣ ደራሲው ራሳቸው ቢያደርጉት ነበር፤ ይሁን እንጂ፣ እድሜአቸው ስለገፋ፣ ረቂቁን መጻፉም ብዙ ጊዜ የፈጀ አታካች ሥራ ስለነበር፣ እሳቸውን ማስቸገሩ እንደ አማራጭ አልተወሰደም፤ ፕሮፌሰር ሽብሩ ፈቃደኛ ስለሆኑ፣ ለእርሳቸው ተሰጠ፡፡ ይህ በዚህ እንዳለ "የኢትዮጵያ አካዳሚ ፕሬስ ቦርድ" ስለ ተቋቋመ፡፡ ቦርዱ የተደነገገውን አዲስ የግምገማ ሥርዓት ተከትሎ ጽሑፉን በሙያተኞች ማስነበብ ነበረበት። ይህም ተጨማሪ ግማሽ ዓመት ገደማ ፈጀ። አዲሱን ሥርዓት ተከትሎ የተስተናገደውም ግምገማ፣ የረቂቅ ጽሑፉን ጠቃሚነት ስለአበሠረ፣ የፕሬሱ ቦርድ

የጽሑፉን መታተም አጸደቀ፡፡ ማሳጠሩን በሚመለከት፣ የመጀመሪያው ሐሳብ ጽሑፉ፣ ካጠረ በኋላ፣ በሁለት ቅጽ ይውጣ የሚል ነበር፤ ይሁን እንጂ፣ ይህ ማለት ሁለት መጽሐፍ እንዲገዛ ስለሚያስገድደው አንባቢን "ማስቸገር" ይሆናል በሚል እሳቤ ተቀይሮ የሚያጥረው ጽሑፍ እንዳለ አንድ መጽሐፍ ሆኖ እንዲወጣ ተወሰነ፡፡ የማሳጠሩ ሥራ ቀላል ተግዳሮት አልነበረም፡፡

የመጀመሪያው ተግዳሮት፣ በማሳጠሩ ሂደት የትኛው ትረካ ይውጣ የትኛው ይቆይ የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ ፕሮፌሰር ሽብሩ አውጥተው አውርደው፣ አንዳንዴም ሙያተኞችን (ለምሳሌ ፕሮፌሰር ሺፈራውን) አወያይተው፣ የሚወጣውን ክፍል ከመረጡ በኋላ ከደራሲው ጋራ መወያየት ነበረባቸው፤ ይሁንና ጸሐፊውን ማግኘት ቀላል አልነበረም፤ ኤምባሲ ውስጥ ተቀማጭ በመሆናቸው፣ ኤምባሲው ባወጣው የጊዜ ሰሌዳ ብቻ ነበር ከወዳጅ ዘመድ ጋር መገናኘት የሚችሉት፡፡ ይህም፣ የሥራውን ሂደት አራዝሞታል፡፡ ሁለተኛ፣ የትርክቱን ፍሰት መጠበቅ ግድ ስለሆነ፣ ከትርክቱ መሀል የተወሰኑ አንቀጾች ወይም ገጾች ሲወጡ፣ ሁለቱን የሚያገናኙ አጫጭር ጽሑፎች መጨመር አስፈላጊ ነበር፤ እነዚህን አጫጭር ጽሑፎች ከዋናው ጽሑፍ ለመለየት ሲባል በአይታሊክስ አድርገናቸዋል፡፡ አይታሊክስ የተመረጠው፣ አንባቢው በቀላሉ እንዲያየው ነው፡፡ ሦስተኛው ተግዳሮት ረቂቁን ተነባቢ ማድረግ ነበር። ረቂቁ የተዘጋጀው እንደ ቀን ተቀን ድርጊት ሆኖ ነበር። ከላይ እንደገለጽነው፣ ይህ የሆነው ደራሲው መጽሐፋቸውን ያረቀቁት፣ በሥራ ላይ በነበሩበት ዘመን፣ የያዙዋቸውን ማስታዎሻዎች ከነናቸው አድርገው ስለነበር ነው፤ ይህም ለመጽሐፉ ትልቅ ዋጋ ቢሰጠውም (የሚያቀርባቸው ሁቆች በዚያ ዘመን እንዳገኛቸው እና እንደወረዱ ስለነበር)፣ አልፎ አልፎ ጽሑፉን ወጥ እና ተነባቢ ለማድረግ የግድ ትረካዎችን ከቦታ ቦታ ማዘዋወር አስፈልጓል። በመጨረሻም ምንም እንኳን ረቂቁ በምዕራፎች ቢከፋፈልም፣ እያንዳንዱ ምዕራፍ ርእስ አልነበረውም። የተለያዩ ትረካዎች በአንድ ምዕራፍ ውስጥ፣ ምንም መከፋፈያ ርእስ እና ንኡስ ርእስ ሳይሰጣቸው ነበር የተተረኩት። እንዲሁም ትረካው ወጥ ሆኖ ለንባብ እንዲያመች ለማድረግ፣ እያንዳንዱ ምዕራፍ በንኡስ ርእሶች ተከፋፍሏል። ይህ ሁሉ የተደረገው ከደራሲው ጋር ተመካክሮ ፈቃዳቸውን በማግኘት ነበር።

እንደዚህ ዓይነት አሰራር (ትላልቅ መጻሕፍትን አሳጥሮ ማቅረብ ወይም abridge ማድረግ)፣ በውጭው የአሳታሚዎች ዓለም የተለመደ አካሄድ ቢሆንም፣ በኢትዮጵያ ግን ገና ሲሠራበት አይታይም፡፡ የአካዳሚው አሳታሚ ፕሬስ ይህንን መንገድ ሲመርጥ ጠቃሚ የሆነውን የኮሎኔል ብርሀኑ ባይህን ጽሑፍ ለሕዝብ ለማድረስ የተሻለው አካሄድ ሆኖ ስላገኘው ነው፤ ሙሉውን ረቂቅ ለማየት የሚፈልግ አንባቢ ወይም ተመራማሪ፣ በአያሌ ጥራዞች የተሰናዱትን ቅጅዎች በኢትዮጵያ ጥናት ተቋም ቤተ መጻሕፍት ወይም በኢትዮጵያ የሳይንስ አካዳሚ ቤተ መጻሕፍት ውስጥ ማግኘት ይችላል፡፡ ይህ አሰራር፣ የአካዳሚው ፕሬስ ምን ያህል ጸሐፊዎች እንዲታተሙላቸው የሚያቀርቧቸውን ጽሑፎች በአክብሮት እና ሙያውን በጠበቀ ጥንቃቄ እንደሚያስተናግዳቸው ያሳያል ብለን እናምናለን፡፡

ይህ ሥራ በተሳካ ሁኔታ ሊጠናቀቅ የቻለው በፕሮፌሰር ሽብሩ ያላሰለሰ ጥረት ስለነበር፣ ፕሬሱ ታላቅ ምስጋና ያቀርብላቸዋል፡፡ ፕሮፌሰር ሽብሩ በብዙ መልኩ ፕሬሳችን እንዲያድግ እና እንዲስፋፋ ያደረጉልንን ትብብር በዚህ አጋጣሚ መጥቀስ እና ባለውለታነታችንን መግለጽ እንወዳለን፡፡ በተጨማሪ፣ ይህ ሥራ እንዲቃና፣ ብዙ ጥረት ያደረጉትን ፕሮፌሰር ሺፈራው በቀለንና የቀድሞውን የፕሬሱን አርታዒ አቶ ብርሃኑ ደቦጭን፣ እጅግ በጣም እናመሰግናለን፡፡

# መግቢያ (የደራሲው)

ይህን የሕይወት ታሪኬን "ያልታሰበው የሕይወቴ ፈታኝ ጉዞ" የሚል ርእስ የሰጠሁት፣ አንደኛ የ2ኛ ደረጃ ትምህርቴን ከአጠናቀቅሁበት ጊዜ ጀምሮ ሕይወቴ እኔ በምፈልገውና በምመርጠው አቅጣጫ ሳይሆን በሌሎች ውሳኔ፣ በሌላ አቅጣጫ ስለተጓዘ፣ ሁለተኛም ይኸው ሕይወቴ የተመራበት አቅጣጫ በብዙ ፈተናዎችና ውጣ ውረዶች የተሞላ በመሆኑ ነው። ያለአግባብ እስራትና ግዞት፣ ቅጣት፣ በጥይት መቁሰል፣ ከሠራዊቱ መባረር፣ እንደገና በተጽዕኖ ወደ ሠራዊቱ መመለስ፣ በከፍሌ ተመርጬ ፖለቲካ ሥራ ውስጥ መግባት፣ በመጨረሻም በአገር ውስጥ ለስደት መዳረግ ደርሶብኛል። ክስና የቅጣት ፍርድም ደርሶብኛል። ዝርዝር ታሪኩ በመጽሐፉ ውስጥ ተገልጿል። ፈታኝ ሕይወት ያሳለፍኩ ለመሆኑ፣ የደርግ አባል ከሆንኩ በኋላ እናቴ "ምርቃት እርግማን ይሆናል?!" በማለት የተናገሩትን መጥቀስ ብቻ በቂ ይሆናል።

ይህን ታሪክ የጻፍኩት በእጄ ከሚገኙ ጥቂት ማስታወሻዎችና በአብዛኛው ሁኔታዎችን በማስታወስ ነው። የማስታወስ ችሎታዬ እኔን ራሴን በጣም አስገርሞኛል። ሴት አያቴ (የአባቴ እናት)፣ ገና በሕፃንነቴ ዓሥር ዓመት ሳይሞላኝ፣ የነገሩኝን ታሪኮች ሁሉ፣ ልክ አሁን እንደነገሩኝ ያህል ነው የማስታውሳቸው። ይህንንም አንባቢው የተባሉትን ታሪኮች መጽሐፉን በሚያነብበት ወቅት ሲያገኛቸው ይበልጥ ይገነዘበዋል ብዬ አምናለሁ። ሌሎችንም ታሪኮች እንደዚሁ በዝርዝር አስታውሳቸዋለሁ። በተለይ በአብዮቱ ወቅት የተከሠቱ ሁኔታዎችን በወቅቱ እንደነበሩ፣ ከእነ ስሜቱ ለማቅረብ ስለፈለግሁ፣ በስብሰባ ላይም ሆነ በተናጠል የተደረጉ ንግግሮችንን እና ክርክሮችን በተቻለ መጠን እንዳሉ ለመግለጽ ሞክሬአለሁ። ሆኖም ንግግሮችን ሙሉ በሙሉ ለማቅረብ፣ ቅደም ተከተላቸውንም ማስታወስ ስለሚያዳግት፣ "ከሞላ ጎደል" የሚል መግለጫ በማስቀደም አስፍሬአቸዋለሁ። ለእኔ ዋናው ቁም ነገር በጊዜው የተደረገው ንግግር ወይም ክርክር ከእነ ስሜቱ መቅረቡ ነው። የአንዳንድ ሰዎችን ስም ቤተሰባቸውን ላለማሳቀቅ ሲባል ለውጬዋለሁ።

መልካም ንባብ።

ብርሃኑ ባይህ እንግዳ (ሌ/ ኮሎኔል)

ይህ ጽሑፍ... ጠቃሚ የሆነ ሰነድ ነው፤ ምክንያቱም እስከ አሁን የማናውቃቸውን ብዙ ነገሮች ስለሚያሳውቀን እና ከዚህ በፊት የምናውቃቸው ጉዳዮች ከሆኑም ስለሚያጠናክራቸው፣ ወይም ስለሚቃረናቸው ነው። መጽሐፉን በሁለት ክፍሎ ማየት ይቻላል። ክፍል አንድ እስከ ደርግ መቋቋም ድረስ ያለው የጸሐፊው ትውስታ ሲሆን፣ ክፍል ሁለት ደግሞ የደርግ ዘመን ይሆናል። ሁለቱም ዋጋ አላቸው። ሁለቱም ክፍሎች ... ለታሪክ ተመራማሪው ብዙ መረጃ ይሰጣሉ። የመጀመሪያው ክፍል ማለትም ቅድመ ደርግ ክፍል ለሁለተኛው ክፍል ታሪካዊ ዐውዱን (historical context) ይሰጠዋል። በዚህ የተነሣ ኋላ ላይ ትላልቅ የፖለቲካ ወይም ወታደራዊ ሥልጣን ይዘው በሀገር ደረጃ ትልቅ ሚና የሚጫወቱ ግለሰቦችን በወጣትነታቸው እናገኝበታለን፡- ጌታቸው ናደው፣ ደምሴ ቡልቶ፣ ተፈሪ ተክለ ሃይማኖት፣ ወዘተ...፡፡ ከጀነራሎችም ቢሆን አንዳንዶቹን ቀድመን እንተዋወቃቸዋለን፡-ጀኔራል አማን ሚካኤል አንዶም፣ ጀኔራል ነጋ ተገኝ ሊጠቀሱ ይችላሉ። ስለዚህ የመጀመሪያው እና የሁለተኛው ክፍል አንድ አምሳል ናቸው ማለት ይቻላል። የዚህ ትውስታ ትልቅ አስተዋጽዖ በስፋት መቅረቡ፣ ብዙ ጉዳዮችን በዝርዝር ማየቱ ነው። ...

- ፕሮፌሰር ሺፈራው በቀለ፣ ለረጅሙ ረቂቅ ጽሑፍ ከሰጡት አስተያየት የተወሰደ

ISBN 978-99944-69-13-0

ዋጋ፡- አራት መቶ ብር ብቻ

Printed @ Eclipse +251 115 572222/23